# Global Storybooks

globalstorybooks.net

## ከቀየዬ ወጥቼ ከተማ ስገባ


✎ Lesley Koyi, Ursula Nafula
Brian Wambi
Dawit Girma



This work is licensed under a Creative Commons Attribution 4.0 International License.
https://creativecommons.org/licenses/by/4.0


# ከቀየዬ ወጥቼ ከተማ ስገባ


✎ Lesley Koyi, Ursula Nafula
Brian Wambi
Dawit Girma


3

አማርኛ am

በመንደራችን ያለው መናሓሪያ በሰዎች እና በታጨቁ አውቶብሶች ተጨናንቆ ነበር። መሬት ላይ ሊጫኑ የተዘጋጁ በርካታ ቁሳቁስ ነበሩ። ረዳቶች አውቶብቸው የሚሄድበትን ቦታ በጩኸት ይጣሩ ነበር።

‹‹ከተማ! ከተማ! ልንወጣ ነው፤ የሞላ!›› እያለ ወያላው ሲጮህ ሰማሁ። አዎ ልሳፈርበት የምፈልገው አውቶብስ ይሄ ነበር።

የከተማ አውቶብሱ እየሞላ ነው፤ ነገር ግን አሁንም ሌሎች ሰዎች ለመግባት ይጋፋሉ። የተወሰኑት እቃቸውን አውቶብሱ ኪስ ውስጥ ይጭናሉ። ሌሎቹ ደግሞ በአውቶብሱ ውስጥ።



ተመላሹ አውቶብስ በፍጥነት እየሞላ ነው። ወዲያው ፊቱን ወደምስራቅ አዞሮ መመለስ ጀመረ። አሁን ለኔ እጅግ አስፈላጊው ነገር አጎቴ የሚኖርበትን ሰፈር ማፈላለግ መጀመር ነው።

ከዘጠኝ ሰዓታት በኋላ ወያላ ወደመጣሁበት መንደር ተመላሽ የሚጓዝ ሰው እየጮኸ ሲጣራ ነቃሁ። ትንሽ ቦርሳዬን ይዤ ከአውቶብስ ወረድኩ።



አዲስ ገቢ መንገደኞች ትኬታቸውን ቶሎ ቶሎ አየት እያደረጉ አውቶብሱ ውስጥ መቀመጫ ቦታ መኖሩን ያያሉ። ህጻኖቻቸውን ያቀፉ ሴቶች ለረጅሙ መንገድ ተመቻችተው ተቀምጠዋል።

በመስኮቱ አጠገብ ጥብቆ ገብቼ ተቀመጥኩ። ከኔ አጠገብ የተቀመጠው ሰው አረንጓዴ የላስቲክ ሻንጣ ይዟል። አሮጌ ነጠላ ጫማ ተጫምቷል፤ ልባሽ ኮት ለብሷል፤ የተበሳጨም ይመስላል።



በመንገዴም አጎቴ በዛ ትልቅ ከተማ የሚኖርበትን ቦታ ስም አስታወስኩ። ሳንቀላፋ ሁሉ ይሄን ስም አነበንባለሁ።

ሃሳቤ ሁሉ ግን ወደቤቴ ነበር። እንደው እናቴ ደህና ትሆን ይሆን? እንደው ጥንቸሎቼስ ገንዘብ ያወጡ ይሆን? ወንድሜስ አስታውሶ ችግኞቼን ውሃ ያጠጣ ይሆን?



በመስኮቱ አሻግሬ እየተመለከትኩ ወዲያው ያደኩበትን መንደሬን እየለቀኩ መሆኑን አስተዋልኩ። ወደ ግዙፍ ከተማ እየተጓዝኩ ነበር።

መኪናው ሞልቷል፤ ሁሉም መንገደኞች ቦታ ቦታቸውን ይዘዋል። ሻጮች አሁንም እየተጋፉ ሸቀጦቻቸውን ለመንገደኞች ለመሸጥ ወደ አውቶብሱ ይገባሉ። ሁሉም ሰው የሚገዛው ነገር ፍለጋ ይሄን ስጠኝ ያን ስጠኝ እያለ ይጯጯህ ጀመር። የሚያደርጉት ነገር ሁሉ ግን እኔን ያዝናናኝ ይዟል።



መንገድ ላይ እየተጓዝን የአውቶብሱ ውስጥ በጣም ይሞቃል። ለመተኛት አስቤ አይኔን ጨፈንኩ።

አውቶብሱ ሲነሳ እኔ በመስኮት በኩል ወደ አፈጠጥኩ። እንደው ወደቀየዬ ዳግም እመለስ ይሆን እያልኩ ተደነቅሁ።



ጥቂቶቹ ተጓዦች የሚጠጣ ነገር ገዙ፣ ሌሎቹ ደግሞ የሚበላ ነገር ገዝተው ይበሉ ጀመር። እንደኔ ምንም ገንዘብ የሌለን ደግሞ ዝም ብለን እንመለከታለን።

ይህ ሁሉ ድርጊት አውቶብሱ የመነሳት ጩኸት ሲያሰማ ረገብ ይላል፤ ሻጮችም ለመውጣት እየተጣደፉ እግረ መንገዳቸውን ፈጠን ፈጠን እያሉ እየተሟሟሁ ይሸጣሉ።



ሻጮቹ ለመውጣት እርስበራሳቸው ይጋፋሉ። አንዳንዶቹ መንገደኞቹን ‹‹አንዴ ልለፍ›› እያሉ ሲወጡ ሌሎቹ ደግሞ ለመሸጥ የመጨረሻ ሙከራ ያደርጋሉ።